የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር

አዲስ ነጋሪ ጋዜጣ

ADDIS NEGARI GAZETA

OF THE CITY GOVERNMENT OF ADDIS ABABA

ሰላሳ ሦስተኛ ዓመት ቁጥር ፻፮
አዲስ አበባ ነሐሴ ፱ ቀን ፳፻፲፯ ዓ.ም.

በአዲስ አበባ ከተማ
ምክር ቤት ጠባቂነት የወጣ

33th Year No.106
Addis Ababa 15th, August 2025

ማውጫ

ደንብ ቁጥር ፻፺፮/፳፻፲፯ የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር የኮሪደር እና የወንዝ ዳርቻ ልማት አስተዳደር ባለሥልጣን ለማቋቋም

የወጣ ደንብ
ገጽ .... ፬ሺ፲፫

CONTENT

REGULATION NUMBER 196/2025 THE ADDIS ABABA CITY GOVERNMENT CORRIDOR AND RIVERSIDE DEVELOPMENT MANAGEMENT AUTHORITY ESTABLISHMENT REGULATION

Page 4013

ደንብ ቁጥር ፻፺፮/፳፻፲፯

የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር የኮሪደር እና የወንዝ ዳርቻ ልማት አስተዳደር ባለሥልጣን ለማቋቋም የወጣ ደንብ

የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር የነዋሪውን ማህበራዊና ኢኮኖሚያዊ ችግሮች ለመቅረፍ፤ ለኑሮ እና ለኢንቨስትመንት የምትመች እንዲሁም አህጉራዊ እና አለም-ዓቀፋዊ ተወዳዳሪ ከተማ እንድትሆን የሚያስችሉ ትውልድ ተሻጋሪ ፕሮጀክቶችንና ፕሮግራሞችን በመንደፍና በመተግበር የበለጸገች ከተማን መገንባት ላይ በመሆኑ፤

የኮሪደር እና የወንዝ ዳርቻ ልማት ሥራዎች ከተማዋን አዲስ ገጽታ በማላበስ ውበትና ጽዳት ከማጎናጸፍም ባሻገር ከባቢያዊ አይበገሬነትና ዘላቂነትን በማረጋገጥና ሰው ሰራሽም ሆነ ተፈጥሮአዊ አደጋዎችን በመግታት ነዋሪው ደህንነቱ በተጠበቀ አካባቢ የመኖር ሕገ-መንግስታዊ መብት ማረጋገጥ አስፈላጊ በመሆኑ፤

REGULATION NUMBER 196/2025 THE ADDIS ABABA CITY GOVERNMENT CORRIDOR AND RIVERSIDE DEVELOPMENT MANAGEMENT AUTHORITY ESTABLISHMENT REGULATION

WHEREAS,the Addis Ababa City Administration is exerting efforts to build a prosperous city through working on and implementing enduring projects and programs that enable to alleviate the social and economic problems of residents of the city, making the city conducive for living and investment as well as creating a city that competes at the continental and international level;

WHEREAS, it has been found necessary to ensure the constitutional right of residents of the city to live in a safe environment beyond creating a new image for the city and making it beautiful and clean through corridor and riverside development works as well as ensuring a resilient and sustainable environment to protect against man-made and natural disasters;

የኮሪደር እና የወንዝ ዳርቻ ልማት ፕሮጀክቶች ዝግጅት፣ ትግበራ፣ አስተዳደር፤ ክትትልና ድጋፍ፣ የነዋሪውን ሁለንተናዊ ተሳትፎና ተጠቃሚነት የማረጋገጥ እና ቀጣይነት ባለው መልኩ የሚያስተዳድር ተቋም ማቋቋም አስፈላጊ በመሆኑ፤

የአዲስ አበባ ከተማ ካቢኔ የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር አስፈጻሚ አካላትን ሥልጣንና ተግባር እንደገና ለመወሰን በወጣው አዋጅ ቁጥር ፹፬/፪ሺ፲፮ አንቀፅ ፺፫ መሠረት ይህን ደንብ አውጥቷል፡፡

ክፍል አንድ
ጠቅላላ ድንጋጌዎች

፩. **አጭር ርዕስ**

ይህ ደንብ "የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር የኮሪደር እና የወንዝ ዳርቻ ልማት አስተዳደር ባለሥልጣን ለማቋቋም የወጣ ደንብ ቁጥር ፻፺፮/፪ሺ፲፯" ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል።

፪. **ትርጓሜ**

የቃሉ ወይም የሐረጉ አገባብ ሌላ ትርጉም የሚያሰጠው ካልሆነ በስተቀር በዚህ ደንብ ውስጥ፡-

፩. **"ከተማ"** ማለት የአዲስ አበባ ከተማ ነው፤
፪. **"ከተማ አስተዳደር"** ማለት የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ነው፤
፫. **"ከንቲባ"** ማለት የአዲሰ አበባ ከተማ ከንቲባ ነው፤
፬. **"ኮሪደር"** ማለት በከተማ አስተዳደሩ መዋቅራዊ ፕላን መሰረት ወይም በከተማ አስተዳደሩ ለመልሶ ማልማት እና ደረጃ ማሻሻል የሚለይ የከተማ ክፍል ነው፤
፭. **"የኮሪደር ልማት"** ማለት በከተማዋ የተመረጡ መንገዶችን ተከትሎ ለከተማዋ ዕድገት አስፈላጊ የሆኑ መሠረተ ልማቶችን በመዘርጋት በቅንጅት ዘላቂና አስተማማኝ በሆነ መንገድ የሚለማበት ተግባር ነው፤
፮. **"የወንዝ ዳርቻ"** ማለት ለወንዝ ዳርቻ መጠበቂያ ቢያንስ ከወንዙ ጠርዝ ግራና ቀኝ ዝቅተኛው ፴ ሜትር ሆኖ እንደ አካባቢው ሁኔታ የከተማ አስተዳደሩ በሚወስነው መሠረት ስፋቱ ሊጨምር የሚችል ሲሆን ለማንኛውም ዓይነት ግንባታ ወይም አገልግሎት እንዲውል የማይፈቀድ ቦታ እና በወንዙ ላይ ተጽዕኖ የሚያሳድር ሥፍራ ነው፤

WHEREAS, it has been found necessary to establish an institution that manages the preparation, implementation, administration and monitoring and supervision activities of the corridor and riverside development projects, ensures the comprehensive participation and benefit of residents as well as its administration in a sustainable way;

NOW, THEREFORE, in accordance with Article 93 of the Addis Ababa City Government Executive Organs Establishment and to Specify the Powers and Duties of the thereof Proclamation Number 84/2023, the Cabinet of the Addis Ababa City Government has issued this Regulation.

PART ONE
GENERAL PROVISIONS

1. **Short Title**

This Regulation may be cited as: "The Addis Ababa City government Corridor and Riverside Development Management Authority Establishment Regulation Number 196/2025."

2. **Definition**

In this Regulation, unless the context requires otherwise:

1. **"City"** means the Addis Ababa city;
2. **"City Government"** means the Addis Ababa City Administration;
3. **"Mayor"** means mayor of the Addis Ababa city;
4. **"Corridor"** means an identified part of the city as per the structural plan of the city or for re-development or upgrading by the city administration;
5. **"Corridor Development"** means an activity where development works are implemented in a coordinated, sustainable, and reliable way on identified roads in the city through carrying out infrastructure development that are necessary for the growth of the city;
6. **"Riverside"** means an area, which is used as a protection for the riverside at least 30 meters from the left and right side of the river edge and its width might increase according to the condition of the areas as per the decision of the city government,that is not allowed for any kind of construction or service and that has an impact on the river;

፯. **“የወንዝ ዳርቻ ልማት”** ማለት በወንዝና የወንዝ ተፋሰስን ተከትሎ የሥነ-ምህዳር ጥበቃ፣ አረንጓዴ ልማት፣ መዝናኛ ቦታዎችን እና ተያያዥ አገልግሎቶችን ከወንዙ ኩታ ገጠም የሆኑ አካባቢዎችን ማልማት ነው፤

፰. **“ባለድርሻ አካላት”** ማለት በኮሪደር ልማት ሥራ በቀጥታም ሆነ በተዘዋዋሪ በልዩ ልዩ መንገዶች እንደየሁኔታው የሚሳተፉ ነዋሪዎች፣ መንግስታዊና መንግስታዊ ያልሆኑ አካላት ናቸው፤

፱. **“አጋር ወይም ተባባሪ አካላት”** ማለት የከተማ አስተዳደሩን የልማትና እድገት ትልሞች ለመደገፍ ከከተማ አስተዳደሩ ጋር በጋራ ለመሥራት የትብብር ስምምነት የሚያደርጉ አለም አቀፍ እና አገር በቀል አካላት ናቸው፤

፲. **“ሰው”** ማለት የተፈጥሮ ሰው ወይም በሕግ የሰውነት መብት የተሰጠው አካል ነው፡፡

፫. <u>**የፆታ አገላለፅ**</u>

በዚህ ደንብ ውስጥ በወንድ ፆታ የተደነገገው የሴትንም ፆታ ያካትታል፡፡

፬. <u>**ዓላማ**</u>

ባለስልጣኑ የሚከተሉት ዓላማዎች ይኖሩታል፡-

፩. የሚለሙ የኮሪደር እና የወንዝ ዳርቻ ልማት መሠረተ ልማቶችን ከዝግጅት እስከ ትግበራ ያሉትን ሥራዎች በመከታተል፣ በማስተባበር እና በማቀናጀት ተፈጻሚ እንዲሆኑ ማስቻል፤

፪. የለሙ የኮሪደር እና የወንዝ ዳርቻ ልማት መሰረተ ልማቶች እና አገልግሎቶች ለታለመላቸው ዓላማ መዋላቸውን እና ተገቢው ጥበቃና እንክብካቤ መደረጉን በመከታተል፣ በመቆጣጠርና ግብረ-መልስ በመስጠት ደህንነታቸውን ማስጠበቅ፤

፫. የለሙ የኮሪደር እና የወንዝ ዳርቻ ልማትን ማስተዳደር እና ቀጣይነት ማረጋገጥ፡፡

7. “Riverside Development” means the development of the areas of a river following the river and its banks including ecological protection, green development, recreational areas, and related services development;

8. “Stakeholders” means residents, governmental and non-governmental organs that directly or indirectly, in various ways, participate in the corridor development activities as per the context;

9. “Collaborative Organs”means international and local bodies that support the development and growth aspirations of the city government and enter into an agreement with the city government to work together;

10. “Person” means a natural or juridical person;

3. <u>**Gender Expression**</u>

In this Regulation, any expression in the masculine gender shall apply to the feminine.

4. <u>**Objective**</u>

The Authority shall have the following objective:

1. Follow up, coordinate, and integrate the corridor and riverside development infrastructures, being carried out, from their preparation to execution stage to realize its completion;
2. Follow up, supervise, and provide feedback to ensure that the developed corridor and riverside development infrastructure and services are used for the intended purpose and appropriate protection and care have been provided to safeguard the thereof;
3. Manage the already developed corridor and riverside developments and ensure its sustainability.

ክፍል ሁለት

መቋቋም፣ አደረጃጀት እና ሥልጣንና ተግባር

፭. **መቋቋም**

፩. የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር የኮሪደር እና የወንዝ ዳርቻ ልማት አስተዳደር ባለስልጣን (ከዚህ በኋላ "ባለስልጣን" እየተባለ የሚጠራ) ራሱን የቻለ የሕግ ሰውነት ያለው የከተማው አስተዳደር አስፈጻሚ አካል ሆኖ በዚህ ደንብ ተቋቁሟል፣

፪. የባለስልጣኑ ተጠሪነት ለከንቲባ ይሆናል፡፡

፮. **የባለስልጣኑ አቋም**

ባለስልጣኑ ፡-

፩. ዋና ዳይሬክተር፣

፪. ምክትል ዋና ዳይሬክተሮች፣

፫. የሥራ ክፍሎችና አስፈላጊ ሠራተኞች እና እንደአስፈላጊነቱ ቅርንጫፎች ይኖሩታል፡፡

፯. **የባለሥልጣኑ ሥልጣንና ተግባር**

ባለሥልጣኑ የሚከተሉት ሥልጣንና ተግባር ይኖሩታል፦

፩. የኮሪደር እና የወንዝ ዳርቻ ልማትን በተመለከተ አዳዲስ እና ወቅታዊ የሆኑ የንድፈ ሀሳብ፣ የግብዓት፣ የአፈጻጸም እና አስተዳደር ስልቶችን ይነድፋል፣ ምክረ-ሀሳብ ለከንቲባው ያቀርባል፣ ሲጸድቅ እንዲተገበር ያደርጋል፣

፪. የሚለሙ የኮሪደር እና የወንዝ ዳርቻ መሰረተ ልማቶችን የሥራ መጠን መረጃዎችን ይይዛል፣ ይተነትናል፣ ለሚመለከታቸው አካላት ያሰራጫል፣

፫. የሚለሙ የኮሪደር እና የወንዝ ዳርቻ ልማት መሰረተ ልማቶች በሚመለከታቸው አስፈጻሚ ተቋማት ተገቢውን ዲዛይን እና ስፔስፊኬሽን መዘጋጀቱን ይከታተላል፣

፬. የኮሪደር እና የወንዝ ዳርቻ ልማትን በተመለከተ የልማት ተነሺዎች ሶሽዮ-ኢኮኖሚ መረጃ የሚሰበሰብበትን ስልት ይቀይሳል፣ አጠቃላይ ተግባሩን ከዝግጅት እስከ ትግበራ ያሉ ሥራዎችን በበላይነት ይመራል፣

፭. የሚለሙ የኮሪደር እና የወንዝ ዳርቻ መሰረተ ልማቶች ሥራዎችን የፊዚካል እና የፋይናንሺያል እቅድ ከአስፈጻሚ ተቋማት ጋር ይገመግማል፣ በተዘጋጁ ዲዛይኖች ጥራት፣ ዋጋ እና ቴክኒክ ላይ ግምገማ እንዲካሄድ ያደርጋል፣

PART TWO

ESTASBLISHMENT, ORGANIZATION, AND DUTIES AND RESPONSIBILITIES

5. **Establishment**
   1. The Addis Ababa City Government Corridor and Riverside Development Management Authority (hereinafter the **"Authority"**) is hereby established as an autonomous executive organ of the city administration having its own legal personality.
   2. The Authority shall be accountable to the Mayor.

6. **Organization of the Authority**

   The Authority shall have:-
   1. A Director-General;
   2. Deputy Director Generals; and
   3. Working departments and the necessary staff as well as branches, as may be necessary.

7. **Powers and Duties of the Authority**

   The Authority shall have the following powers and duties:
   1. Generate new and up-to-date designs, implementation, and management strategies regarding the corridor and riverside development; present proposals to the mayor; implement same upon approval;
   2. Maintain and analyse information regarding the extent of the corridor and riverside development infrastructures to be carried out; distribute same to the concerned organs;
   3. Follow up that the relevant design and specification are prepared for the corridor and riverside development infrastructures, to be undertaken, by the concerned executive organs;
   4. Design strategies to gather the socio-economic information of those individuals who are vacated due to the corridor and riverside development; superiorly lead the overall activities of the thereof from preparation to the implementation stage;
   5. Evaluate the physical and financial plan of the corridor and riverside infrastructural works, to be undertaken, with that of the executive organs; ensure that the quality, price, and technical aspects of the prepared designs are evaluated;

፮. በኮሪደር እና የወንዝ ዳርቻ ልማት ሥራዎች ዙሪያ የሚሰማሩ ድጋፍ የሚሰጡ አመራሮችን፣ የባለድርሻ እና አጋር አካላትን ያቀናጃል፤ ያስተባብራል፤

፯. በኮሪደር እና በወንዝ ዳርቻ ልማት የለሙትን መሰረተ ልማቶች፣ አገልግሎቶች እና አገልግሎት መስጫዎችን በባለቤትነት ይቆጣጠራል፤ ያስተዳድራል፤

፰. የዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፯) ድንጋጌ ቢኖርም በኮሪደር እና በወንዝ ዳርቻ ልማት ውስጥ ከለማው መሠረተ ልማት፣ የአገልግሎት መስጫ ህንጻ፣ የመናፈሻ ወይም የመዝናኛ ግንባታ መካከል በባለሥልጣኑ መተዳደር የማይገባቸውን ራሱ በሚያወጣው መስፈርት መሠረት ይለያል፤ ለከንቲባው ያቀርባል፤ ሲወሰን ለሚያስተዳድራቸው አካላት ያስረክባል፤ ይከታተላል፤ ይቆጣጠራል፤

፱. የአካባቢ ልማት ፕላን በፀደቀላቸው የኮሪደርና የወንዝ ዳርቻ ቦታዎች ላይ በዕቅድና በዝርዝር ዲዛይን ያልተደገፈ ግንባታ እንዳይኖር ወይም እንዳይካሄድ ይከታተላል፤ ይቆጣጠራል፤ ጥፋት ተፈጽሞ ሲገኝ ሕጋዊ እርምጃ እንዲወሰድ ስልጣን ላለው አካል ያቀርባል፤ አፈጻጸሙን ይከታተላል፤

፲. የድጋፋዊ ሱፐርቪዥን እና ክትትል ሥርዓት ይዘረጋል፤ ተግባራዊነቱን ይከታተላል፤ ያረጋግጣል፤

፲፩. የኮሪደር እና የወንዝ ዳርቻ ልማት ሥራዎችን ከሚመለከታቸው አስፈጻሚ ተቋማት ጋር በመቀናጀት በቪዲዮ፣ በፎቶ፣ በካርታ፣ በድረ-ገጽ እና በመሳሰሉት የመረጃ መያዣ ዘዴዎች እንዲሰነዱ ያደርጋል፤ ልምዶችን ይቀምራል፤

፲፪. የኮሪደር እና የወንዝ ዳርቻ ልማት ሥራዎችን ከሚመለከታቸው አስፈጻሚ ተቋማት ጋር በመቀናጀት ለአገር ውስጥ እና ለውጭ ጎብኝዎች ያስተዋውቃል፤ ያስጎበኛል፤ ልምድ ያካፍላል፤

፲፫. ከሚመለከታቸው አስፈጻሚ አካላት ጋር በመቀናጀት የለሙ የኮሪደርና ወንዝ ዳርቻ ልማቶች ጥበቃ፣ ጽዳት፣ እንክብካቤ እና ጥገና እየተደረገ መሆኑን ያረጋግጣል፤ ግብረ-መልስ ይሰጣል፤ አስፈላጊ ማስተካከያ መደረጉን ያረጋግጣል፤

6. Integrate and coordinate those leaders, stakeholders, and partners working in connection with the corridor and riverside development works;

7. Control and manage the established infrastructures, services, and service providing facilities that are developed around the corridor and riverside development areas;

8. Notwithstanding to the provision of Sub-Article (7) of this Article, identify infrastructures, service providing buildings, parks, and recreational area facilities that are developed by the corridor and riverside development, which will not be included under the management of the authority as per the criteria it shall set forth; present same to the mayor; handover same to a body that will manage them; follow up and control same;

9. Follow up and control that constructions without plans and detailed designs will not be carried out on the corridor and riverside development areas with an approved environment development plan; while encountering offences, present it to the relevant organ to ensure that legal measures are taken; follow up the execution of same;

10. Establish a support-oriented supervision and monitoring system; follow up and ensure its implementation;

11. Make sure that the corridor and riverside development works are documented with videos, photos, maps, websites, and other similar information storage mechanisms in collaboration with the concerned executive organs; organize experiences;

12. Promote the corridor and riverside development works for local and foreign tourists in collaboration with the concerned executive organs; facilitate tours and share experiences;

13. Ensure that protection, cleaning, care, and repairing is being done for the developed corridor and riverside developments in collaboration with the concerned executive organs; provide feedback; make sure that necessary remedies are taken;

፲፬. የለሙ የኮሪደር እና የወንዝ ዳርቻ ልማት መሰረተ ልማቶች በለሙበት አግባብ ስታንዳርዳቸው ተጠብቆ ሳይበላሹ ባሉበት ለታለመላቸው አገልግሎት መዋላቸውን ያረጋግጣል፤

፲፭. ዓላማውን ለማሳካት የሚረዱ ሌሎች ተዛማጅ እና በከተማው ከንቲባ የሚሰጡትን ሌሎች ተግባራትን ያከናውናል፤

፲፮. የከተማ አስተዳደሩን የአስፈጻሚ አካላትን ሥልጣንና ተግባር ለመወሰን በወጣው አዋጅ የተዘረዘሩ የወል ሥልጣንና ተግባር ይኖሩታል፡፡

፰. <u>የባለሥልጣኑ ዋና ዳይሬክተር ሥልጣንና ተግባር</u>

የባለሥልጣኑ ዋና ዳይሬክተር የሚከተሉት ሥልጣንና ተግባር ይኖሩታል፡-

፩. ዋና ዳይሬክተሩ የባለሥልጣኑ ዋና ሥራ አስፈጻሚ በመሆን ሥራዎችን ይመራል፤ ያስተዳድራል፤

፪. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፩) የተደነገገው እንደተጠበቀ ሆኖ፡-

ሀ) በዚህ ደንብ አንቀጽ ፯ የተመለከቱትን የባለሥልጣኑን ሥልጣን እና ተግባራት በሥራ ላይ ያውላል፤

ለ) የባለስልጣኑን ድርጅታዊ መዋቅር ከሚመለከታቸው አስፈጻሚ ተቋማት ጋር በመሆን አዘጋጅቶ ለከንቲባ ያቀርባል፤ ሲወሰን ሥራ ላይ ያውላል፤

ሐ) በከተማ አስተዳደሩ የመንግሥት ሠራተኞች ሕግ መሠረት ሠራተኞችን ይቀጥራል፤ ያስተዳድራል፤ ያሰናብታል፤

መ) በከተማ አስተዳደሩ የመንግሥት ሠራተኞች የሥራ መደቦች ምዘና፣ ደረጃዎች ምደባና የደመወዝ ስኬል ደንብ መሠረት የአስተዳደሩን የፋይናንስ አቅም ያገናዘበ የባለስልጣኑን ሠራተኞች ደመወዝና ማንኛውም ጥቅማ ጥቅሞች አጥንቶ ለከንቲባ ያቀርባል፤ ሲፈቀድ ተግባራዊ ያደርጋል፤

ሠ) የባለሥልጣኑን ዓመታዊ ዕቅድና በጀት ያዘጋጃል፤ ሲጸድቅ ሥራ ላይ ያውላል፤

ረ) በተፈቀደለት በጀትና የሥራ ዕቅድ መሰረት ገንዘብ ወጪ ያደርጋል፤

14. Ensure that the developed corridor and riverside development infrastructures are preserved as per their standard and used for the intended purpose without damage;
15. Carry out other activities given by the mayor and activities that help to attain its objectives;
16. The authority shall have the collective power and duties specified for the executive organs of the city administration as per the Proclamation of the Addis Ababa City Government Executive Organs Establishment and to Specify the Powers and Duties of the thereof.

8. **<u>Power and Duties of the Director-General of the Authority</u>**

The Director-General of the authority shall have the following powers and duties:

1. The Director-General shall act as the chief executive officer of the authority and lead and manage activities of the thereof;
2. Without prejudice to the provision of Sub-Article (1) of this Article:

A. Exercise the powers and duties of the authority specified under Article 7 of this Regulation;

B. Prepare the organizational structure of the authority in collaboration with the concerned executive organs and submit it to the mayor; implement same upon approval;

C. Employ, administer, and dismiss employees in accordance with the civil service laws of the city administration;

D. Conduct a study regarding the salary and any benefits of the employees of the authority according to the job position evaluation, grading, and salary scale Regulation of the civil servants of the city administration by taking the financial capacity of the administration into consideration and submit it to the mayor; implement same upon approval;

E. Prepare the annual budget and work plan of the authority; implement same upon approval;

F. Effect payments according to the approved budget and work plan;

ሰ) ከሦስተኛ ወገን ጋር በሚያደርጋቸው ግንኙነቶች ባለሥልጣኑን ይወክላል፤

ሸ) የባለሥልጣኑን የሥራ ክንውን እና የሂሳብ ሪፖርቶች አዘጋጅቶ ለከንቲባ እና ለሚመለከተው አካል ያቀርባል፤

ቀ) ለባለሥልጣኑ የሥራ ቅልጥፍና በሚያስፈልግ መጠን ከስልጣንና ተግባሩ በከፊል ለባለሥልጣኑ ምክትል ዋና ዳይሬክተር በውክልና ሊያስተላልፍ ይችላል፡፡

፱. **<u>የምክትል ዋና ዳይሬክተር ሥልጣንና ተግባር</u>**

፩. የባለሥልጣኑን ተግባራት በማቀድ በማደራጀት፣ በመምራትና በማስተባበር ዋና ዳይሬክተሩን ያግዛል፤

፪. በዋና ዳይሬክተሩ ተለይተው የሚሰጡ ተግባራትን ያከናውናል፤

፫. ዋና ዳይሬክተሩ በማይኖርበት ጊዜ ዋና ዳይሬክተሩን ወክሎ ይሠራል፡፡

<u>ክፍል ሦስት</u>

<u>በጀት እና የሂሳብ መዛግብት</u>

፲. **<u>የበጀት ምንጭ</u>**

የባለሥልጣኑ በጀት፡-

ሀ) ከከተማው አስተዳደር የሚመደብ በጀት፣

ለ) በከተማው አስተዳደር በኩል ከሀገር ውስጥ ወይም ከውጭ ሀገር አጋር አካላት የሚሰጥ የድጋፍ በጀት፣ እና

ሐ) ከልዩ ልዩ ሕጋዊ ምንጮች ከሚገኝ ፈንድ፤ ይሆናል፡፡

፲፩. **<u>የሂሳብ መዛግብት</u>**

፩. ባለሥልጣኑ የተሟሉና ትክክለኛ የሆኑ ሂሳብ መዛግብትን ይይዛል፤

፪. የባለሥልጣኑ የሂሳብ መዛግብትና ገንዘብ ነክ ሰነዶች በዋናው ኦዲተር ወይም እሱ በሚሰይመው ኦዲተር በየዓመቱ ይመረመራል፡፡

<u>ክፍል አራት</u>

<u>ልዩ ልዩ ድንጋጌዎች</u>

፲፪. **<u>የባለድርሻ ቅንጅት እና ተሳትፎ</u>**

፩. በከንቲባ የሚመራ የኮሪደር እና የወንዞች ዳርቻ ልማት ግብረ-ኃይል ይቋቋማል፤ ስትራቴጂካዊ እና ቴክኒካዊ አመራር ይሰጣል፤

G. Represent the authority in its dealings with third parties;

H. Prepare the work performance and financial reports of the authority and present same to the mayor and the relevant organs;

I. May delegate part of his powers and duties to the Deputy Director-General to the extent necessary for the effective performance of the activities of the authority.

9. **<u>Power and Duties of the Deputy Director-General</u>**

1. Assist the Director-General in planning, organizing, and leading the activities of the authority;
2. Carry out activities that are specifically identified by the General-Director;
3. Act as the General-Director in his absence.

<u>PART THREE</u>

<u>BUDGET AND BOOKS OF ACCOUNTS</u>

10. **<u>Budget Source</u>**

1. The budget source of the Authority shall be:

A. A budget allocated by the city government;

B. A support budget obtained from local or foreign partners through the city government;

C. Various legally obtained funds.

11. **<u>Books of Accounts</u>**

1. The Authority shall maintain complete and accurate books of accounts.
2. The books of accounts and financial documents of the Authority shall be audited annually by the Auditor-General or an auditor assigned by him.

<u>PART FOUR</u>

<u>MISCELLANEOUS PROVISIONS</u>

12. **<u>Stakeholders Collaboration and Participation</u>**

1. A taskforce, to be led by the Mayor, for the corridor and riverside development shall be established; it provides strategic and technical leadership;

፪. ባለሥልጣኑ ለከንቲባው በማቅረብ የሚያስወስናቸውን የኮሪደር እና የወንዞች ዳርቻ ልማት ትግበራ ንዑሳን ኮሚቴዎችን ያደራጃል፣ ያስተባብራል፤

፫. በዚህ ደንብ መሠረት በኮሪደር እና የወንዝ ዳርቻ ልማት ባለድርሻ የሆኑ ወይም ተሳትፎ ማድረግ ያለባቸውን የከተማ አስተዳደሩ የአስፈጻሚ ተቋማት ሚና እና ቅንጅታዊ አሰራርን በተመለከተ ባለሥልጣኑ ዝርዝር የአሰራር መመሪያ ያዘጋጃል፤ ለከንቲባ ያቀርባል፤ ይሁንታ ሲያገኝ ተግባር ላይ ያውላል፤

፲፫. **ስለአስፈጻሚ ተቋማት ኃላፊነት**

፩. በዚህ ደንብ መሠረት የኮሪደር እና የወንዝ ዳርቻ ልማት የሚተገብር የከተማ አስተዳደሩ አስፈጻሚ ተቋም በሕግ በተሰጠው ሥልጣንና ተግባር መሰረት የኮሪደር እና የወንዝ ዳርቻ ልማትን ተግባራዊ ለማድረግ ከባለሥልጣኑ እና ከሌሎች አስፈጻሚ ተቋማት ጋር በቅንጅትና በትብብር መስራት ይኖርበታል፤

፪. በዚህ ደንብ አንቀጽ ፲፬ የተዘረዘሩት እና በቅንጅታዊ ሥራ እንዲሳተፉ በከንቲባ የሚወሰኑ ሌሎች የአስተዳደሩ አስፈጻሚ ተቋማት ስለኮሪደር እና የወንዝ ዳርቻ ልማት ለባለስልጣኑ ሪፖርት የማቅረብ፤ ግብረ-መልስ የመቀበል፤ በተሰጠው ግብረ መልስ መሰረት የማስተካከያ ወይም የእርምት እርምጃ የመውሰድ ኃላፊነት አለባቸው፤

፫. በዚህ ደንብ አንቀጽ ፲፬ የተዘረዘሩት የሚመለከታቸው አስፈጻሚ ተቋማት በኮሪደርና ወንዝ ዳርቻ ልማት ጥናት፣ ዕቅድ፣ ዲዛይን እና ትግበራ ሂደት የተሟላ ተሳትፎ የማድረግ እና ባለሥልጣኑ በሚሰጠው ግብዓት መሠረት የማስተካከል ኃላፊነት አለባቸው፤

፬. በሚለሙ ወይም በለሙ የኮሪደር እና የወንዝ ዳርቻ የመሠረተ ልማት ላይ የሚሳተፍ ማንኛውም ሰው በቅድሚያ የባለሥልጣኑን ይሁንታ የማግኘት ግዴታ አለበት፡፡

2. Organize and coordinate sub-committees for the implementation of the corridor and riverside development that the authority submits to the mayor and gets approval;
3. The Authority shall prepare a detailed directive regarding stakeholders involvement or the role of the executive organs of the city government that will participate in the corridor and riverside development activities and coordination procedures as per this Regulation; present same to the Mayor; implement same upon approval.

13. **Responsibilities of Executive Organs**

1. According to this Regulation, an executive organ of the city government that, as per the powers and duties given to it by the law, implement the corridor and riverside development should work in collaboration and coordination with the authority and other executive organs to carry out the corridor and riverside development.
2. Executive organs of the city government that are listed under Article 14 of this Regulation and others that will participate in the coordination work as per the decision of the Mayor shall have a responsibility to submit reports to the authority, receive feedback, and take corrective measures based on the given feedback concerning the corridor and riverside development;
3. Executive organs of the city government that are listed under Article 14 of this Regulation shall have the responsibility to fully participate in the study, planning, designing, and implementation phases of the corridor and riverside development and make adjustments as per the inputs given by the authority;
4. Any individual who will participate in the on-going or finalized corridor and riverside development projects shall have the obligation to obtain the consent of the authority first.

፲፬. **<u>ባለ ድርሻ አስፈጻሚ ተቋማት</u>**

የኮሪደር እና የወንዝ ዳርቻ ልማትን ከእቅድ እስከ ትግበራ በሕግ በተሰጣቸው ሥልጣንና ተግባር መሠረት የሚፈጽሙ እና የሚያስፈጽሙ የአስተዳደሩ አስፈጻሚ ተቋማት፡-

፩. የሥራና ክህሎት ቢሮ፣
፪. የፋይናንስ ቢሮ፣
፫. የፕላንና ልማት ቢሮ፣
፬. የከተማ ውበትና አረንጓዴ ልማት ቢሮ፣
፭. የትራንስፖርት ቢሮ፣
፮. የመሬት ልማትና አስተዳደር ቢሮ፣
፯. የቤቶች ልማትና አስተዳደር ቢሮ፣
፰. የዲዛይንና ግንባታ ሥራዎች ቢሮ፣
፱. የኢኖቬሽንና ቴክኖሎጂ ልማት ቢሮ፣
፲. የኮሙኒኬሽን ቢሮ፣
፲፩. የሴቶች፣ ህጻናትና ማህበራዊ ጉዳይ ቢሮ፣
፲፪. የወጣቶችና ስፖርት ቢሮ፣
፲፫. የባህልና ኪነጥበብ ቢሮ፣
፲፬. የቱሪዝም ኮሚሽን፣
፲፭. የመንገዶች ባለሥልጣን፣
፲፮. የውሃና ፍሳሽ ባለሥልጣን፣
፲፯. የግንባታ ፈቃድና ቁጥጥር ባለሥልጣን፣
፲፰. የኤሌክትሪክ አገልግሎት አስተዳደር ባለሥልጣን፣
፲፱. የትራፊክ ማኔጅመንት ባለሥልጣን፣
፳. የአካባቢ ጥበቃ ባለሥልጣን፣
፳፩. የደንብ ማስከበር ባለሥልጣን፣
፳፪. የህዝብ መዝናኛ ቦታዎች አስተዳደር ኮርፖሬሽን፣
፳፫. የጽዳት አስተዳደር ኤጀንሲ፣
፳፬. የመንግስትና የግል አጋርነት ጽህፈት ቤት፣
፳፭. የክፍለ ከተማ እና የወረዳ አስተዳደር ዋና ሥራ አስፈጻሚ ጽህፈት ቤቶች፣
፳፮. ሌሎች እንደ አስፈላጊነቱ በከንቲባ የሚለዩትን ያካትታል፡፡

፲፭. **<u>የመተባበር ግዴታ</u>**

፩. በዚህ ደንብ አንቀጽ ፲፬ ስር የተዘረዘሩ የአስተዳደሩ አስፈጻሚ ተቋማት ይህንን ደንብ ለማስፈጸም በሚወጣው መመሪያ መሠረት ሚናቸውን የመወጣት፤ እና

14. **<u>Stakeholder Executive Organs</u>**

The following are the executive organs that will execute or cause the execution of the corridor and riverside development from the planning to the implementation phase according to the power and duties entitled to them as per the law:

1. Labour and Skill Bureau;
2. Finance Bureau;
3. Plan and Development Bureau;
4. City Beautification and Green Development Bureau;
5. Transport Bureau;
6. Land Management and Administration Bureau;
7. Housing Development and Management Bureau;
8. Design and Construction Works Bureau;
9. Innovation and Technology Development Bureau;
10. Communication Bureau;
11. Women, Children, and Social Affairs Bureau;
12. Youth and Sports Bureau;
13. Culture and Arts Bureau;
14. Tourism Commission;
15. Roads Authority;
16. Water and Sewerage Authority;
17. Construction Permit and Regulatory Authority;
18. Electric Service Management Authority;
19. Traffic Management Authority;
20. Environmental Protection Authority;
21. Code Enforcement Authority;
22. Public Recreational Areas Management Corporation;
23. Cleansing Management Agency;
24. Public Private Partnership Office;
25. Offices of the Chief Executive Officers of the sub-cities and woredas;
26. Other organs identified by the mayor, as deemed necessary.

15. **<u>Duty to Cooperate</u>**

1. Executive organs of the city government that are listed under Article 14 of this Regulation are obliged to carry out their role as per the directive to be issued for the implementation of this Regulation; and

፪. በባለሥልጣኑ የሚሰጡ ተግባራትና የማስተካከያ ሀሳቦችን ተቀብሎ የመተግበርና ሪፖርት የማድረግ ግዴታ አለባቸው፤

፫. ማንኛውም ሰው ይህንን ደንብ ለማስፈጸም የመተባበር ግዴታ አለበት፡፡

፲፮. ተጠያቂነት

፩. ባለሥልጣኑ በዚህ ደንብ መሠረት በኮሪደርና በወንዝ ዳርቻ ልማት ዙሪያ በሚያደርገው የማቀናጀት፣ የማስተባበር፣ የመከታተል፣ የመቆጣጠር ወይም በመፈጸም ሂደት ጥፋት ፈጽሞ የተገኘ የአስፈጻሚ ተቋም ኃላፊ ላይ አስተዳደራዊ እርምጃ እንዲወሰድ ለከንቲባ ያቀርባል፤

፪. የዚህን ደንብ ድንጋጌ የጣሰ ማንኛውም ሰው እንደአግባብነቱ በፍትሐ-ብሔር፣ በወንጀል፣ በአስተዳደር ሕግ ወይም በሁሉም ተጠያቂ ይሆናል፡፡

፲፯. ተፈፃሚነት ስለማይኖረው ሕግ

ይህን ደንብ የሚቃረን የከተማው አስተዳደር ካቢኔ ያወጣው ደንብ፣ መመሪያ ወይም የከተማው አስተዳደር አስፈጻሚ ተቋማት ያወጧቸው መመሪያዎች ወይም ልማዳዊ አሰራር በዚህ ደንብ ውስጥ በተሸፈኑ ጉዳዮች ላይ ተፈፃሚነት አይኖራቸውም፡፡

፲፰. መመሪያ የማውጣት ሥልጣን

ባለሥልጣኑ ይህን ደንብ ለማስፈጸም ከንቲባውን በማማከር መመሪያ ሊያወጣ ይችላል፡፡

፲፱. ደንቡ የሚፀናበት ጊዜ

ይህ ደንብ ከነሐሴ ፱ ቀን ፪ሺ፲፯ ዓ.ም ጀምሮ የፀና ይሆናል፡፡

አዲስ አበባ ነሐሴ ፱ ቀን ፪ሺ፲፯ ዓ.ም

አዳነች አቤቤ ደሳ
የአዲስ አበባ ከተማ ከንቲባ

2. The executive organs are also obliged to accept activities and corrective measures given by the authority and implement same as well as report;
3. Any individual shall be duty bound to cooperate to execute this Regulation.

16. Accountability

1. The authority shall report to the mayor for the taking of an administrative measure against a head of an executive organ who commits an offence in its efforts to integrate, coordinate, follow up, control the corridor and riverside development or implementation phase of the thereof as per this Regulation;
2. Any individual who violates the provisions of this Regulation shall be held liable as per the civil code, penal code, administrative laws, or with all the relevant laws.

17. Repealed Laws

Any Regulation and directive issued by the cabinet of the city administration or directives or customary practices issued by the executive organs of the city administration which are inconsistent with this Regulation shall have no effect.

18. Power to Issue Directives

The authority may, by consulting the mayor, issue directives for the implementation of this Regulation.

19. Effective Date

This Regulation shall enter into force as of this 15th day of August 2025.

Done at Addis Ababa, this 15th day of August 2025.

AdanechAbiebie Dessa
Mayor of Addis Ababa City